የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ

# ሳምንታዊ ጋዜጣ

Purpose Black ETHIOPIA

2015 ግንቦት ቅጽ 1 ቁጥር 13

## ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የተሠማራባቸው ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች በጋራ ተመጋግበው ለኩባንያው ስኬት ቁልፍ ሚና እንደሚኖራቸው ተገለጸ።

የኑሮ ውድነትን ታሪክ ማድረግን እና የትጉሁን ገበሬ ሕይወት መቀየርን ዋና ዓላማው አድርጎ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው በዋነኝነት በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር (Kegeberew Integrated Extention Program) በኩታ ገጠም እርሻ(cluster farm) ኢንቨስትመንት የተሰማራው ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ በ5 ዓመት ውስጥ በአጠቃላይ 1 ሚሊዮን ገበሬዎችን በኩታ ገጠም የእርሻ ሥርዓት ለማካተት ባቀደው መሠረት ይህን ታላቅ ግብ ለማሳካት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ ተገለጸ።

በአንድ ኩታ ገጠም እርሻ ውስጥ 100 ገበሬዎች የሚያካትተው የከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር የታቀዱትን 1 ሚሊዮን ገበሬዎች በመርሐግብሩ ለማቀፍ በአጠቃላይ 10 ሺህ ኩታ ገጠም እርሻ (Cluster farm) እንደሚያስፈልገው ይፋ መሆኑ ይታወሳል።





በመርሐግብሩ አንድ የኩታ ገጠም እርሻን ለማደራጀት 33.7 ሚሊዮን ብር እንደሚፈጅ እና በአጠቃላይ የሚኖሩት 10 ሺ እርሻዎች ወጪ 337 ቢሊዮን ብር መሆኑን ባከናወነው የአዋጭነት ጥናትያሳወቀው የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የስትራቴጂክ ዕቅድ እና ቢዝነስ ልማት ክፍል በከገበሬው የተቀናጀ የግብርና ማስፋፊያ መርሐግብር ለኩታ ገጠም እርሻው (Cluster farm) ትግበራ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሟላት እና ውጥኑን ለማሳካት የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ነድፎ ባንኮች በፕሮጀክቱ ኢንቨስት ማድረግ የሚያስችላቸውን (Commercial Agricultural Clusters Financing Platform) የተሰኘ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰሻ መድረክ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝም ታውቋል።

ባንኮች በኩታ ገጠም እርሻ(Cluster farm) ኢንቨስትመንቱ ለሚያደርጉት ተሳትፎ ዋስትና የሚሆናቸውን ገንዘብ ደግሞ በሌላኛው እና የኑሮ ውድነትን ታሪክ ከማድረግ አንጻር እጅግ ከፍተኛ ሚና በሚኖረው በTSM ፕሮጀክት በኩል ለማሰባሰብ ዕቅድ መያዙን የገለጸው ኩባንያው ይህ TSM የተሰኘ ፕሮጀክት በውስጡ እጅግ ዘመናዊ እና ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ ባለ115 ወለል ሁለገብ ሕንጻ/ታወርን ጨምሮ ለመኖሪያ፣ ለንግድ፣ ለመዝናኛ፣ እና ለሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ግንባታዎች የተካተቱበትና አጠቃላይ ወጪውም 70 ቢሊዮን ብር መሆኑ ይታወሳል።

የTSM ፕሮጀክቱ በግንባታ ሒደት ላይ ሆኖ ለሥራ ማስኬጃ ከተያዘው በጀት ላይ 20 ቢሊዮን ብሩ ኩባንያው በኩታ ገጠም እርሻው (Cluster farm) ኢንቨስት በማድረግ እንዲሳተፉ (Commercial Agricultural Clusters Financing Platform) በተሰኘው መድረክ ለሚሳተፉት ባንኮች ዋስትና(Collateral Scheme) በመሆን ከፍተኛ ወለድ በሚያስገኝ ዝግ አካውንት ተቀማጭ የሚደረግ ሲሆን ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያም ያሉትን ፕሮጀክቶች አንደኛውን ከሌላኛው ጋር በማቆራኘት የኑሮ ውድነትን ታሪክ የማድረግ እና የትጉሁን ገበሬ ሕይወት የመለወጥ ራዕዩን እንዲያረጋግጥ የሚያስችሉት መሆናቸውም ተገልጿል።

## የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ምርት ክምችት ክፍል ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የግብርና አግሮፕሮሰሲንግና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለሸማቹ ማኅበረሰብ ለማቅረብ በትኩረት እንደሚሠራ አስታወቀ።

በኩባንያው የምርት አቅርቦት ክፍል አማካኝነት ለክምችት የሚመጡ ምርቶችን ጥራት በመፈተሽ እና በጥንቃቄ በመያዝ በሁሉም የፐርፐዝ ብላክ የምርት ስርጭት ክፍሎች የሚያዳርሰው የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ምርት መጋዘን የከገበሬውን ምርቶች ለሸማቹ ማኅበረሰብ በማድረስ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያበረከተ ይገኛል ሲሉ የምርት ክምችት ክፍል ዳይሬክተር ወ/ት ኤቨን እስክንድር ገልጸዋል።

ክፍሉ በዋናነት ከገበሬው ሱቆች፣ ከሆቴሎችና ሌሎችም የንግድ ተቋማት እንዲሁም ከከገበሬው ኢኮሜርስ የሚመጡ የምርት ፍላጎቶችን የማሟላት ተግባር የሚያከናውን ሲሆን ወደ መጋዘን የሚገቡና ከመጋዘን የሚወጡ ምርቶችን በሚገባ በመቆጣጠር በሚቀርቡ ትዕዛዞች መሠረት ለሸማች የሚደርሱበትን ሁኔታ ያመቻቻል ያሉት ወ/ት ኤቨን ምርቶችን ተቀብሎ በጥንቃቄ ከማቆየት፣ ከመለየት ብሎም ከማሰራጨት በተጨማሪ ጥራታቸውን ያልጠበቁ ምርቶች ወደ አቅራቢዎች ተመላሽ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራዎችም በክፍሉ አማካኝነት እንደሚተገበሩ አብራርተዋል።


ምስል በነብዩ ዳንኤል

“

**ምርቶች በብልሽት ምክንያት እንዳይወገዱ ለማድረግ በምርት ክምችት ክፍሉ ምን ምን ሥራዎች ተከናውነዋል ስንል ላቀረብንላቸው ጥያቄም በጥራታቸው ደረጃ ከመመደብ ባሻገር በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸጡ ሰፊ ተግባራት መከናወናቸውን በማስረዳት ባለፉት 9 ወራት ብቻ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያለው ምርት በ ሁለተኛ የጥራት ደረጃ እንዲሸጥ መደረጉን አስታውሰዋል።**

ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፉት 9 ወራት 101 ሚሊዮን ብር የሚገመቱ የግብርና ምርቶች እንዲሁም ከ18 ሚሊዮን ብር በላይ ግምታዊ ዋጋ ያላቸው የኢንዱስትሪ ምርቶች ወደዋናው መጋዘን መግባታቸው እና ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ለሱቆች እና ለከገበሬው ኢኮሜርስ መሰራጨቱ ተገልጿል።

የTCTዝብላክ ኢትዮጵያ የምርት ክምችት ክፍል ኃላፊ ኩባንያው ከምርት አቅራቢዎችና አምራቾች እንዲሁም ከበርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በጋራ መሥራት ችሏል ያሉ ሲሆን ጥራታቸውን የጠበቁ የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶችን እንዲሁም የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽዖዎችን በየቀኑ ወደ ዋናው መጋዘን በማስገባት በቂ የሆነ የምርት መጠን እንዲኖር ብሎም ለሸማቹ እንዲደርስ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች መከናወናቸውን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ከመቼውም ጊዜ በተለየ ኩባንያው በምርቶች ጥራት ላይ ትኩረቱን ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ የገለጹት ኃላፊዋ በሁሉም ምርቶች ላይ በብቁ ባለሙያዎች እና የጥራት መመዘኛዎች የምርት ጥራት ቁጥጥር እንደሚከናወንም አስታውቀዋል።


በሎጂስቲክስ፣ ጥራት ቁጥጥር እና ሌሎችም ዘርፎች ለዜጎች በርካታ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር የቻለው የከገበሬው ምርት ክምችት ክፍል በስሩ 143 ሠራተኞችን የሚያንቀሳቅስ ሲሆን በ3 የሥራ ፈረቃ መሥራት የሚችሉበትን ስርዓት መዘርጋቱንም አስረድተዋል።

ሠራተኞች በ3ቱም ፈረቃዎች ሲገቡም ሆነ ሲወጡ መገልገል የሚችሉባቸው የመታጠቢያና የትራንስፖርት አቅርቦት መሟላቱን የገለጹት ወ/ሪት ኤቨን የመመገቢያ ስፍራ ተገንብቶ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን አስታውሰው በቀጣይም ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ለሸማቹ ማኅበረሰብ ለማድረስ ዘመናዊ የሆኑ አሠራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ይበልጥ ለማቀላጠፍ የምርት ክምችት ክፍሉ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

## በከገበሬው ታወር 100 ካሬ ላይ የሚያርፉ ባለ 3 መኝታ ቤቶችን በ1.5 ሚሊዮን ብር ብቻ መሸመት የሚቻልበት ልዩ የ15 ቀን ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ።

ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ የጥቁርን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ልዕልና እውን ለማድረግ ከወጠናቸው ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ በሆነውና የከገበሬው ታወር ባለአክሲዮን ሞዴል(TSM) በተሰኘው ተነሣሽነት ሥር በዓለማችን እጅግ ዘመናዊ እና ተወዳዳሪነት ካላቸው ኪነ-ሕንጻዎች መካከል አንዱ የሚሆነውን ባለ115 ወለል ታወር ግንባታ ለማከናወን እንቅስቃሴ ላይ መሆኑ ይታወቃል።

ለመኖሪያ፣ ለመዝናኛ፣ ለገበያ፣ እና ለሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ግንባታዎች በተካተቱበት በዚህ ግዙፍ ፕሮጀክት ከሚገነቡት የመኖሪያ አፓርትመንቶች መካከል 100 ካሬ ላይ የሚያርፉትን ባለ 3 መኝታ ቤቶች እስከ ሰኔ 06 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ለሚሸምቱ ሁሉ እጅግ አስደናቂ ሊባል በሚችል የዋጋ ተመን አንድ ባለ 3 መኝታ አፓርታማ በ1.5 ሚሊዮን ብር ብቻ ለሽያጭ መቅረባቸውን የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ይፋ ካደረጉበት ዕለት አንስቶ ደንበኞች ወደ ፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና መሥሪያ ቤት በአካል በመምጣት የእድሉ ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኝ ተገልጿል።



“

**ግንቦት 21 ቀን 2015 ዓ.ም በተጀመረው በዚህ ዘመቻ በታቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ 1 ቢሊዮን ብር የማሰባሰብ ዕቅድ መያዙን ያወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው አከፋፈሉን በተመለከተም ሸማቾች አሁን ላይ ቅድሚያ ክፍያ 1 ሚሊዮን ብር የሚፈጽሙ ሲሆን ቀሪውን 500 ሺህ ብር በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ ከወለድ ነጻ በሆነ ሥርዓት እንዲያከናውኑ እንደሚደረግ ከዚያም ባለፈ ሸማቾች የTCTዝብላክ ባለአክሲዮን መሆን የሚችሉበት እድል መመቻቸቱንም አብራርተዋል።**

ዋና ዓላማውን ዘላቂነት ባለው ሁኔታ በልዩ የአክሲዮን ሥርዓት ኩባንያው ለተሠማራባቸው የግብርና ሥራዎች ገቢ መሰብሰብ ያደረገው የ Tower Shareholder Model ፕሮጀክት ተገንብቶ ሲጠናቀቅ በየዓመቱ ፐርፐዝብላክ ከገበሬው ሕይወት መሻሻል እና ኑሮ ውድነትን ታሪክ ከማድረግ አንጻር በኩታ ገጠም ኢንቨስትመንት ለሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎች በየዓመቱ ከ5 እስከ 7 ቢሊዮን ብር ካፒታል ሊያስገኝ የሚችል መሆኑን የገለጹት ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ ያዘጋጀው የኩባንያው ባለአክሲዮን እና 100 ካሬ ላይ የሚያርፍ የባለ3 መኝታ ቤት አፓርትመንት ባለቤት መሆን የሚያስችል ዕድል በማስታወቂያ ዋጋ መቅረቡን አውስተዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው አክለውም ኩባንያው የወጠነውን የታወር ፕሮጀክት ለማስጀመር የተዘጋጀው ይህ አጭር የኢንቨስትመንት ዕድል የተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ አክሲዮኑም ሆነ መኖሪያ አፓርትመንቱ በገበያ ዋጋ እንደሚሸጡ ከዚያም ባለፈ አክሲዮንና መኖሪያ አፓርትመንት በጋራ የሚሸጡበት ልዩ ዕድልም ለውስን ጊዜያት ብቻ የሚዘልቅ መሆኑን ተናግረዋል።

ቀደም ሲል በወርኀ ጥር በተካሔደው የኩባንያው የባለአክሲዮኖች አጠቃላይ ጉባኤ ላይ በተወሰነው መሠረት የኩባንያው አጠቃላይ የገንዘብ አቅም 5 ቢሊዮን ብር ሲሞላ አንድ አክሲዮን የመግዣ ዋጋው በሦስት እጥፍ አድጎ ቀደም ሲል ከነበረበት 1 መቶ ብር ወደ 3 መቶ ብር የሚያድግ መሆኑን ያስታወሱት የፐርፐዝብላክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ፍስሐ እሸቱ በተዘጋጀው ልዩ እድል ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል፣ ባለሀብቶች እና ድርጅቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።




| የሽያጭ ግዜ | የሽያጭ ዋጋ | አከፋፈል | |
|---|---|---|---|
| | | ቅድምያ | ቀሪ በ 5ዓመት |
| ግንቦት 21 - ሰኔ 6 | 1,500,000 | 1,000,000 | 500,000 |
| ሰኔ 7 - ሰኔ 20 | 3,500,000 | 2,500,000 | 1,000,000 |
| ሰኔ 21 - ሐምሌ 4 | 6,500,000 | 4,000,000 | 2,500,000 |
| ሐምሌ 5 - ሐምሌ 29 | 9,000,000 | 6,000,000 | 3,000,000 |
| ከሐምሌ 30 በኋላ | 35,000,000 | 15,000,000 | 20,000,000 |



ዋና አዘጋጅ፡ ሰላማዊት ደበበ
ሲንየር ሪፖርተር፡ ጌታባለው ገ/ሐና
ሪፖርተር፡ ኤደን ደነቀ

ለበለጠ መረጃ
ሰንጋተራ ነጋዴዎች ህብረት ህንጻ 5ተኛ ፎቅ
+251-946-545454/
+251-925922222/
+251-925822222
7151
www.purposeblackethiopia.com

